# "ሦስቱ መለሶች "

ከሙሉቀን 9/3/12

'መለስ አንድ ሰው ብቻ አይደለም፤ መለስ ብዙ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ ሰው አጣች።' ያናገርኳቸው አንድ አባት አይናቸው እምባ እያቀረረ የተናገሩት ነበር። በሰአቱ ያናገርኳቸውን አባት የልብ ስብራት እያሰብኩኝ ቆየሁና በርግጥም ኢትዮጵያ ብዙ ሰው ነው ያጣችው . . . በማለት ለራሴ ማረጋገጫ ሰጠሁ።

የአስተያየት ሰጪውን አባት ንግግር መላልሼ ሳሰላስለው ጠ/ሚ/ሩ በርካታ እንደነበሩ ታወሰኝ ስለክቡር ጠ/ሚ/ር መለስ ስብእና፣ ግለ-ባህርይ እና አኗኗር ባሻገር ግን ቢያንስ ሶስት አይነት መለሶችን መግለፅ እችላለሁ።

**የነፃነት ታጋዩ መለስ**

መለስን እና የትግል አጋሮቻቸውን ወደ በረሃ የሰደዳቸው የሽፍትነት አምሮት አሊያም ጀብደኝነት አይደለም ጠ/ሚ/ሩ የታገሉት እና በኋላም የጣሉት የደረግ ስርአት ኢትዮጵያ በዘመኗ ካጋጠሟት አመራሮች በአይነቱ የተለየ እና የከፋ ነበር። ስርአቱ የዜጐችን የብሔር የሐይማኖት፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነት የነፈገ ከመሆኑም በለይ እናቶች ድጋሜ ላለመውለድ ስለት እስከማድረግ የደረሱበት አሰቃቂም ጭምር ነበር።

የመለስና አጋሮቻቸው የትጥቅ ትግል ደርግን ብቻ ሳይሆን ዘመንን ነበር ድል የነሳው። ያ ዘመን ወጣቱ የተፈጀበት፣ ርሃብ እና ስደት የነገሰበት የሰብአዊ መብት ጥሰት ህጋዊ የነበረበት እና የልማት እንቅስቃሴዎች ቆመው 'ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር' የተባለበት ነበር። የነፃነት ታጋዮ መለስ ያንን ዘመን ድል ነስተው ለተዋጉለት የኢትዮጵያ ህዝብ ዘመን የማይሽረው ውድ ስጦታ አጐናፅፈዋል። የአቶ መለስ አስተዳደር አገሪቱ ከደርግ ስርአት ነፃ ከወጣችበት ማግስት ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዘመናት በአምባገነን መሪዎቹ የተነጠቃችውን ሰብአዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና ፖለቲካዊ መብቶቹን መልሶ አጐናፅፏቸዋል።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ህዝቦች በብሔራዊ ማንነታቸው አይሸማቀቁም፤ ሃይማኖታዊ ስርአታቸውን በአደባባይ ከመከወን አይታቀቡም፤ ፖለቲካዊ አመለካከታቸውን ማራመድም ሆነ መደራጀት በጥይት አያስፈጃቸውም ዛሬ በኢትዮጵያ ዜጋ መሆን ብቻውን ዋስትና ሆኗቸው ዜጐች በሰላም ወጥተው መግባት እንዲችሉ የመለስ ዜናዊ እና የትግል አጋሮቻቸው መስዋእትነት የወለደው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት የነፃነት ታጋዩን መለስ ወደ በረሃ ያስገቧቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለሳቸው ማረጋገጫ ነው። አርበኝነት ጥቂቶች ብቻ የሚታደሉት ፀጋ ነው። ከራሳቸው ግላዊ ፍላጐት በዘለለ ስለ ሰፊው ህዝብ የነፃነት ፍላጐት ተጨንቀው ነፍጥ በማንሳት የአንበሳ ክርን ያለውን ስርአት ለመታገል የቻሉ እና የተሳካላቸው እጅግ ጥቂት አርበኞችን ብቻ ነው አለማችን ያየችው።

ከጥቂት አርበኞች መካከል የተደላደለ ትምህርታቸውን በመተው ለነፃነት ታጋይነት የነብስ ጥሪያቸው ምላሽ ለመስጠት ነፍጥ አንግተው በረሃ የገቡትን ታጋይ መለስ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ በሞት ቢጣያቸውም ባወረሱት ውድ የነፃነት እና የፍትህ ስርአቶች ለዘላለም ይዘክራቸዋል።

**ዲፕሎማቱ መለስ**

ከ17 አመቱ እልህ አስጨራሽ ትግል በላይ የመለስን ጉልበት የፈተነው የደረግ ስርአት ያፈራረሰው የአገሪቷን የውጪ ግንኙነት ማደሱ ነበር። በአፄ ሀይለ ስላሴ ዘመን አገሪቷ በአፍሪካ እና በተቀረው አለም ተፅእኖ ፈጣሪ ለመሆን ያስቻላት የውጪ ግንኙነት ምስረታ ነበር። የወታደራዊው መንግስት በህዝባዊ አብዮት የንጉሱን ስርአት ባፈረሰበት ማግስት ነበር አገሪቷን ከወዳጆቿ በመለየት መናኛ ስርአት መንግስት /hermit kingdom/ የመሰረተው። የቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ሰለባ የሆነው የደርግ ስርአት በቀድሞዋ ሶብየት ህብረት ተፅእኖ ስር በመውደቅ ንጉሱ ለአመታት በገለልተኛ ፖለቲካ /non-alignment/ አካሔዳቸው ያፈሯቸውን ምእራባዊ ወዳጆች በማግለል አገሪቷን የምስራቁ ጐራ ጥቅም አስፈፃሚ አደረጋት።

ከደርጉ የፖለቲካዊ አመለካከት ለውጥ በላይ አገሪቷ ባጋጠሟት ተደጋጋሚ ርሃብ፣ ድርቅ እና ስደት እንዲሁም ለአመታት የዘለቀ ጦርነት የተነሳ ለዘናመት የገነባችውን አለማቀፋዊ ክብርና ሞገስ አጣች። በመለስ ፈታኝ አመታት /1984 -1990/ ውስጥ የአገሪቷን ወዳጆች መመለስ፣ የሻከሩ ጐረቤታዊ ግንኙነቶችን ማደስ፣ የተበላሸ አገራዊ ገፅታን መገንባት እና ኢትዮጵያ ያጣችውን አህጉራዊ እና አለማቀፋዊ ተሰሚነት የመመለስ ተግባራት ከትጥቅ ትግሉ በላይ ፈትኗቸዋል። ለፈተና አዲስ ያልሆኑት መለስ ይሄኛውንም ፈተና በአንፀባራቂ ድል ተወጥተው የአገሪቷን ክፍለ አህጉራዊ እና አህጉራዊ የዲፕሎማሲ የበላይነት በአስተማማኝ መሰረት ላይ ገንብተዋል። ኢትዮጵያ የራሷን ችግር በፍጥነት በመፍታት ለአህጉራዊ ሰለም እና መረጋጋት እንዲሁም የጋራ ብልፅግና ግንባር ቀደም አንቀሳቃሽ መሆን መቻሏ የመለስ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ያስገኘው ውጤት ነው።

መለስ ከአገራቸው አልፈው የአህጉር አፍሪካን የማያልቅ የእርስ በርስ ግጭትና ስር የሰደደ ድህነት ለመፍታት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ ሰርተዋል። መንግስታቸው ከደርግ ውድቀት በኋላ እትብቱ ሳይደርቅ ነበር ለሩዋንዳ እና ብሩንዲ ውስጣዊ ችግር ቤዛ የሆነው። መላው አለም ለአፍሪካ ጀርባውን በሰጠበት በዚያ ዘመን የመለስ ኢትዮጵያ ውድ ልጆቿን ወደ ሁለቱ አገራት በመላክ በአህጉሩ ታይቶ የማያውቀውን ዘግናኝ ጭፍጨፌ ማስቆም ችላለች።

በሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ላይቤሪያ፣ ሶማሊያ እና ሱዳን የሰላም ማስከበር ተልእኮ ጐን ለጐን አህጉራዊ የግጭት አፈታት ስርአትን ማሳየት የቻሉት አቶ መለስ በተደጋጋሚ የአፍሪካ የቁርጥ ቀን መሪ መሆናቸውን አሳይተዋል። የመለስ ጥልቅ ዲፕሎማሲያዊ እውቀት ከታየባቸው በርካታ ሁኔታዎች መካከል የምስራቅ አፍሪካ አገራትን የውስጥ ሰላም ለማረጋገጥ በሽምግልና፣ በአደራዳሪነት በአወያይነትና በገላጋይነት በመሳተፍ በቀጠናው ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ያደረጋቸው ጥረቶችና ስኬቶቻቸው የበርካቶችን ልብ እንዲገዙ አስችሏቸዋል።

የመቶ ሺዎችን ህይወት የቀጠፈው የደቡብ እና ሰሜን ሱዳን የአመታት ጦርነት እንዲያበቃ ባደረጉት ብርቱ ጥረት የሚወደሱት ጠ/ሚ/ር መለስ ከደቡብ ሱዳን ነፃነት በኋላ በሁለቱ አገራት መካከል የተነሳውን የግዛት ይገባኛል ግጭት ለመፍታት ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል። ሁለቱ ሱዳኖች በሚጋጩበት አቢዬ ግዛት ሰላም አስከባሪ ጦር ከመላክ ጀምረው ሁለቱን መሪዎች ወደ አዲስ አበባ በመጥራት ግጭቱን በሰላም እንዲፈቱ

ያደረጉት ዲፕሎማሲያዊ ጥረት በሁለቱ ሱዳኖች መካከል የተቀጣጠለውን ጦርነት በእንጭጩ ለማስቆም አስችሏል።

ለአመታት ሰላም በማጣት በጉሳ ግጭትና ሽብር ስትታመስ ለነበረችው ሶማሊያ የመለስ ዲፕሎማሲያዊ ጥረት የማይተካ ውለታና አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ ለአመታት መንግስት አልባ በመሆን ለቀጠናው ሰላም ስጋት በነበረችው ሶማሊያ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም አስችለዋል። ሶማሊያውያን የራሳቸውን ችግር ያለ ምንም አይነት የውጪ ጣልቃ ገብነት በራሳቸው የሚፈቱበትን መንገድ ለመፍጠርም የሚመለከታቸውን ወገኖችና የአለም አቀፍ ማህበረሰብ በማስተባበር አመርቂ ውጤት አስገኝተዋል። የመለስ ዲፕሎማሲ የሶማሊያን የሽሽግግር መንግስት መልሶ ለማቋቋም ከማስቻሉ በላይ ለደካማው መንግስት ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ለሱማሌ ህዝብ አገራችን ኢትዮጵያ ያላትን ሁለንተናዊ ወዳጅነት ለማሳየት ችለዋል። ዲፕሎማቱ መለስ ከክፍለ አህጉሩ ተፅእኖዋቸው በተጨማሪ ለአመታት በሱዳንና ግብፅ የበላይነት ስር የወደቀውን የአባይ ተፋሰስ የውሃ ፖለቲካ ሰብሮ በመግባት ኢትዮጵያ በወንዞቿ መጠቀም የምትችልበትን እውቅና ለማግኘት ችለዋል።

በውሃ ፖለቲካው መለስ አገራቸው ከድህነት ለመላቀቅ ወንዞቿን ለልማት ማዋል ግድ እንደሚላት የተፋሰሱን አገራት ማሳመን ችለዋል። የመለስ የውሃ ፖለቲካ ዲፕሎማሲ ሁሉንም የተፋሰስ አገራት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚችል መሆኑን በማሳየትም በታችኛው የተፋሰስ አገራት ተቀባይነት ማግኘት ችለዋል። ዲፕሎማቱ መለስ የመላው አፍሪካ መሪ የ3ኛው አህጉራዊ ድሃ ማህበረሰብ ወኪል ነበሩ። አፍሪካን በበርካታ አለም አቀፍ ጉባኤዎች የወከሉት አቶ መለስ ስለ አህጉሩ ሁለንተናዊ ብልፅግና እና መጻኢ እድል ለአለም ተናግረዋል። ለአህጉራዊ ውክልናቸው ጠ/ሚ/ር መለስ አፍሪካ በአለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርአት ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታጣ ተሟግተዋል። የአህጉሪቷን ተሰሚነት ከፍ ለማድረግም ከሃያላን የአለማችን አገራት እና ህብረቶቻቸው ጋር ተደራድረዋል።

የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወደ አፍሪካ ህብረት ሲሸጋገር የለውጡ ዋና ተዋናይ የነበሩት መለስ ከአህጉራዊ ህብረቱ ምስረታ ጋር በተያያዘ የህብረቱ መቀመጫ አዲስ አበባ ሆኖ እንዲቀጥል ከበርካታ የአፍሪካ መሪዎች ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገዋል። በስኬታቸውም አዲስ አበባን የአፍሪካ መዲና የአህጉሩ የፖለቲካና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማእከል ማድረግ ችለዋል። በመለስ ዲፕሎማሲያዊ ስኬት ዛሬ አዲስ አበባን በአለም ቀዳሚ የዲፕሎማሲ ማእከል ከሆኑ ሦስት ወይም አራት ከተሞች መካከል አንዷ እንድትሆን አስችለዋታል፡፡ በዚህም ከመቶ በላይ ኤምባሲዎች የበርካታ አለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች እና ቢሮዎች መቀመጫ ሆናለች። ለበርካታ አለም አቀፍና አህጉራዊ ስብሰባዎች ተመራጭ የሆነችው አዲስ አበባ የመለስ ዲፕሎማሲያዊ ስኬት ማሳያ ነች።

**ህዳሴ አብሳሪው መለስ . . .**

ሶስተኛው መለስ የቀድሞ ሁለቱ መለሶች ውጤት ነው ሊባል ቢችልም ይሔኛው መለስ የራሱ የሆነ መገለጫዎች አሉት። አንድ አገር ለዘመናት ከማቀቀችበት የጨለማ ዘመን ወደ እድገትና ብልጽግና የምታደርገው ሽግግር “ህዳሴ” ይባላል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ማነቆ ተይዛ ስሟ ከድህነት ርሀብ፣ ድርቅ እና የእርስ በርስ ጦርነት ጋር አብሮ ሲጠቀስ ኖሯል። ይሔንን ስር የሰደደ ችግር ነቅሎ ለመጣል እና አዲስ የተስፋ ብርሃን ማሳየት የህዳሴ አብሳሪው መለስ ፈታኝ ስራ ነበር። በትጥቅ ትግሉ እና በዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴው ያካበቱትን  ልምድና የአመራር ጥበብ  በመጠቀም ለአገሪቱ ሁለንተናዊ ሽግግር ብርሃን የፈነጠቁት መለስ በህዳሴ አብሳሪነታቸው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሲዘክራቸው ይኖራል።

ለሃያ አንድ አመታት በመሯት ኢትዮጵያ ቀድሞ ታይተው የማያውቁ ፖለቲካዊ ለውጦችን ለአለም ለማሳየት ችለዋል፡፡ ከፖለቲካዊ ህዳሴዎቻቸው መካከል የኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታ የሰጠውን ህገ መንግስት እውን ማድረግ የመለስ ዘለአለማዊ ስኬት ነው። ሕገመንግስቱ የቀጣይ ፖለቲካዊ ስርአት መሰረት ሆኖ እንዲቀጥል ማስቻል ደግሞ የባለቤቱ የኢትዮያ ህዘብ ሃላፊነት ነው። በኢትዮጵያ ነፃ ፍትሃዊና  ወቅቱን የጠበቀ ምርጫ መካሔድ፤ የመረጃ ነፃነትን መጐናፀፍ፤ የግልና የህብረተሰብ ነጻ አመለካከቶችን ማንሸራሸር፤ መደራጀትና የመንግስት አሰራርን መቃወም፤ ነፃ የመረጃ አገልግሎት /ፕሬስ/ መመስረት ከአመታት በፊት ፈፅሞ የማይታሰቡ ነበሩ። እነዚህ ስኬቶች የመለስ እና  የአጋሮቻቸው የትግል ውጤቶች መሆናቸውን የሚክድ የለም።

ኢኮኖሚያዊ ህዳሴን በተመለከተ  በዲማክራሲያዊ ህገ መንግስቱ ባሰፈሩት የኢኮኖሚያዊ መብቶች የተበረታቱ ኢትዮጵያውያን በአገራቸው አንጡራ ሃብቻውን በማፍሰስ ለራሳቸውና ለወገናቸው ጠቃሚ  ስራን መስራት ችለዋል። የመለስ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የውጪ አገራት በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን በማፍሰስ የጋራ ተጠቃሚነታቸው ለማሳየት ችሏል። በውጤቱም በርካታ የውጪ ባለሃብቶች ወደ ኢትዮጵያ በመግባት የአገሪቷን እድገት በማፋጠን ረገድ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ አስችለዋል። የመለስ ዜናዊ ሶስት እንቀስቃሴዎች ኢትዮጵያን ከወደቀችበት አንስቷታል። ሶስቱ መለሶች ለአመታት በሯን ዘግታና ተነጥላ የነበረችውን ኢትዮጵያ ቀና በማድረግ ማንነቷን ለቀሪው አለም እንድታሳይ አስችሏታል። ሶስቱን መለሶች ኢትዮጵያና የመላው አፍሪካ ህዝብ ከልቡ አያወጣቸውም። የመለስ ዲፕሎማሲያዊ ልፋት  ውጤት በማስገኘቱ ዛሬ ኢትዮጵያን በይበልጥም በአፍሪካ አህጉርና እንዲሁም በተለያዩ ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ላይ  ተፅእኖ ፈጣሪ  ሃይል አድርጓታል።

ዘመንን ድል የነሳ እና ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን የሰራ ጀግና “ሞተ” አይባልም። ምክንያቱም “መለስ ብዙ ነው” አዎ መለስ በበርካታ ቦታዎች የሚታይ ስኬት ነው። የመለስ መንፈስ የፅናቱ ልጆች በሆኑ የኢትዮጵያ ዜጐች እና በለፋላቸው አፍሪካዊ ወገኖች ልብ ውስጥ ለዘላለም ሲታወስ ይኖራል።